

# ግዜ

ገደብ የሌለው ስሌት
አሻራ አይጥል ምልክት
አዲስ ቀን ነኝ መጣሁ ወራት
ልቀይር ነው ይህን ዓመት
ብሎ አይነፋ መለከት!

ልክ እንደ እኛ ቃል አይገባ
ግዜ እሚሉት እቅድ አልባ

ችቦ አይለኩስ መድፍ ጥይት፤
ደውል የለው ለምልክት

መጀመሪያው አይታወቅ
መደምደሚያውን ብንናፍቅ
ፀጥ ያለ ነው መዘውሩ
አይሞት ግዜ ህያው ዘሩ
እኛ ግና ዘመነ አጭር
ደቂቃ ሰዓት ስንቆጥር
ይኸው ደሞ አዲስ ዓመት
ከተፍ አለ ዛሬ ለሊት

ደረጀ 2010 

This PDF was created using the PDF Converter Elite software.
To remove this watermark, please license this product at www.pdfconverter.com

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot*. ***You may contact Dereje Mekonen for comments at*** drj_mekonen@yahoo.co.uk.